ፓኖራማ ቁጥር 75

የትዝብት አድማስ

ሐምሌ 19 ቀን 2001 ዓም

## ዐባይ ጠፍቶ እንዳያስጠፋን

"ተናግረን ነበረ ማማ ላይ ወጥተን ÷
የወያኔን ወንጀል ቀደም ብለን አይተን÷
ሰሚ በመጥፋቱ መዝግበን አስቀመጥን÷
ለታሪክ ለትውልድ ይጠቅም እንደሁ ብለን ። "

ከዚህ በታች የሰፈረውን ሐተታ ከአራት ዓመታት በፊት በጥር 4 1997 ዓም (ጃንዋሪ 12 ቀን 2005) መዝግበን በፍኖተ ዲሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ አማካኝነት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሰማታችንን እናስታውሳለን ። በተለያዩ ድረ- ገጾችም እንዲታተም ተደርጎ ነበር ።ዛሬ ይህንን ሐተታ በድጋሜ ለማቅረብ የፈለግንበት ምክንያት ÷ የወያኔ አገዛዝ ባለፈው ሳምንት የዓባይን ወንዝ አስመልክቶ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ የክህደት ተግባር በመፈፀሙ ነው።

በዐባይ ተፋሰስ አካባቢ የሚገኙ 11 የአፍሪካ ሀገሮች የፓርላማ አባላት ባለፈው ሳምንት ኮንጎ ላይ ተሰብስበው ÷ የዐባይን ወንዝ ግብፅ የብቸኛ ተጠቃሚ እንድትሆን ያደረጓትን የ1929ና የ1959 ዓም ስምምነቶች ለሌሎች የዐባይ ተፋሰስ ሀገሮችም እንዲጠቅም መሆን ይገባዋል ብለው ያቀረቡትን ኃሳብ ግብፅ በመቃወሟ ምክንያት÷ጉዳዩን ለዓለም ፍርድ ቤት ለማቅረብ የወሰዱትን ውሳኔ ÷ የወያኔ ሰዎች ከግብፅ ጋር ተመሳጥረው ÷የኢትዮጵያን መብትና ጥቅም አሳልፈው ሰጥተዋል ። ይህ ከህደታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ አላስገረመውም ። ይህንን በመቃወም ÷ ኢሕአፓ በሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓም / ጁላይ 22 2002 መግለጫ አውጥቷል ። መግለጫውን ከዚህ ሐተታ ጋር በአባሪነት አቅርበናል። ይህን ማድረጋችን ÷ ለታሪካዊ ማስረጃ ሰነድ እንዲሆን በማለት ነው።

## የትዝብት አድማስ

ጥር 4 ቀን 1997 ዓም

## ዐባይ ጠፍቶ እንዳያስጠፋን

ለአለፉት ሠላሳ ዓመታት የግብፅ የሳይንስ ጠቢባንን በሀገራቸውናና በውጭ ሀገሮች የኑክሌር ምርምርና ሙከራ ሲያካሂዱ እንደቆዩ፥ ዘ ዋሽንግቶንን ፖስት የተሰኘው የአሜሪካ ጋዜጣ በጃንዋሪ 5 ቀን 2005 ዓም ባወጣው ዕትሙ አስፍሮታል። የዓለም አቀፍ አውቶሚክ ኃይል ድርጅት በበኩሉ፥ በግብፅ መንግሥት ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኑክሌር ምርምር ጥናት ተቋም፥ እስከ አሁን ድረስ ምንን ውጤት እንዳስመዘገበ አይታወቅም ብሏል። ግብፅ፥የአውቶሚክ መሳሪያን ለመስራት ምኞት ያላት መሆኗ ቢታወቅም፥ እስከ አሁንን ድረስ ግን፥ ኒኩላርን ለመስራት የሚያስችሉ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን፤ ማለትም፥ ዩራኒየምና ፕሉቶኒየም የተሰኙትን ንጥረ ነገሮችን አዳብራ ለማከማቸት ምንን ያህል ችሎታ እንዳላት በትክክል የሚናገር የለም። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ሳይንትፊክ ጆርነናል በተሰኘው መጽሄታቸው፥ የግብፅ የኒኩሌር ሳይንቲስቶች ባወጡት ዜና ለማወቅ እንደተቻለው፥ የግብፅ የኑክሌር ኃይል ምርምርና ሙከራ፥ በግብፅ መንግሥት ቁጥጥር ስር እንዳልሆነ ለመሸፈን ጥረዋል። የዓለም አቀፍ የኑክሌር ኃይል ድርጅት ቃል አቀባይ ሚስተር ማርክ ግዋዝዲክ በበኩላቸው ፥ በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል።

የኒኩሌር ጦር መሳሪያ ለመገንባት ይጠቅማል የሚባለው ዩሬንየም ኮምፓውንድ ሙከራ ግብፅ፣ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር፣ ከ1970 እስከ 1980 በነበሩት ዓመታት እንዳደረገች ግን ተረጋግጧል። ግብፆች፣ እነኝህን ሙከራዎች ያደረጉት በፈረንሳይና በቱርክ ውስጥ እንደሆነ የሚጠቁሙ ዜናዎች አሉ። ይህን ዜና አስመልክቶ፣ የዋይት ሐውስና የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ቃለ አቀባዮች ፣ ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ተናግረዋል። ግብፅ፣ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር፣ በ1982 ዓም የኒኩሌር መሳሪያ መጠቀም የሚያግደውን ስምምነት የፈረመች ሀገር ብትሆንም ፤ የኑክሌር ሳይንስ ጠበብቶቿ ግን በኒኩሌር ሥራ የተሰማሩ ሙከራውም እያደረጉ መሆናቸው ተደርሶበታል። ይህ ዜና ደግሞ፣ የኑክሌር መሳሪያ መስራት የሚከለክለውን ስምምነት ከመፈረሟ ጋር የሚፃረር ሆኗል በማለት ተመልካቾች ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ግብፅ እስካሁን የኒኩሌርን ምርመራ አስመልክቶ ምን ያህል ጉዞ ለመሄድ

እንደቻለች የሚመረምረው መርማሪ ቡድን ፣የሥራው ውጤት በሚቀጥሉት የየካቲት መጋቢት ወሮች ይፋ እንደሚያደርግ ይጠበቃል:: ለጉዳዩ ቅርበት ያለቸው የዓለም የኒኩሌር ሳይንስ ጠቢባንና ዲፕሎማቶች፣ እንደሚናገሩት፣ የግብፅ የኑክሌር ፕሮግራም ደረጃ፣ ከኢራን ፣ ከሰሜን ኮርያ፣ ከሊቢያ ወይም ከደቡብ ኮሪያ ጋር የሚስተካከል አይሆንም ይላሉ:: መሥሪያ ቤቱ በኦስትርያ ወይም ነምሳ ዋና ከተማ በቪዬና ያደረገው፣ የዓለም አቀፍ የአዎቶሚክ ኃይል ድርጅት ድሬክተር የሆኑት፣ግብፃዊው ሞሃመድ ኤልባራዲ ይህ ዜና ሊያሳስባቸው እንደሚችል፣ አንዳንድ ታዛቢዎች ቢጠቁሙም፣ በኢራክ ጉዳይ ከአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጋር ባላቸው ቅራኔ የተነሳ፣ ለሦስተኛ ጊዜ እንዳይመረጡ አሜሪካ ሙከራ ተዳርጋለች ተብሎ ይታመናል::

ግብፅ የኑክሌር መሳሪያ ባለቤት ለመሆን የምታደረገው ጥረት ዜና ፣ ከማነኛቸውም ሀገሮች በላይ ሊያሳስባት የሚችለው ፥ እርሷን ኢትዮጵያን እንደሚሆን አርቆ አስተዋይ ለሆነው ዜጋ ሁሉ የሚሳነው አይሆንም:: ምናልባት ግብፅ የዚህ መሳሪያ ባለቤት የምትሆንበት ጊዜ በርካታ ዓመታት የሚፈጅ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻል ይሆናል:: ያም ቢሆን ግን ኢትዮጵያ የግብፅን የኒኩሌር ፕሮግራም ሂደት በአርምሞ ልታየው የሚገባት ልትሆን አይቻላትም:: እንዲያው ይህን አረፍተ ነገር ለማስፈር የተገደድነው፣ ለእግር መንገዳችን መግቢያ፣
እንዲሆነን ብለን እንጅ አጣዳፊና አንገብጋቢ ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው ሌላ ዐብይ ጉዳይ አለ:: እኛ ኢትዮጵያውያ ስለ ኑክሌር ኃይልም ይሁን አጠቃቀም ከማለማችን ወይም ከመጨነቃችን በፊት፣ ሌሎች የሚያሳስቡና እንቅልፍ የማያስወስዱ ብርቱ ጉዳዮች አሉ :: ሀገራችን ቀስ በቀስ እየጠፋች ወደ ከርሰ መቃብሯ ከመግባቷ አስቀድሞ፣ እርሷን ማዳን ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ብለን አናምናለን:: ይህ ዕምነት ደግሞ፥ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት መሆኑ፣ ማንም ሊጠራጠር አይቻለውም:: የሀገርን መኖር የሚተካው አንዳችም ጉዳይ ሊኖር ስለማይችል፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ማለት የሚያስፈልግ አይሆንም::

እረ ለመሆኑ ከዛሬ ስድሳና ሰባ ዓመታት በፊት ግብፅና ኢትዮጵያን በምን ደረጃ ላይ ነበሩ? ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፍፃሜ ማግስት፣ ሁለቱም የነበሩበት ሁለንተናዊ ሁኔታ ከሞላ ጎደል የተራራቀ ነበር ማለት አይቻልም:: በተለይም ከመንግሥት አስተዳደርና ከባዕዳን ተጽዕኖ አኳያ በተመሳሳይ ደረጃ ነበሩ ቢባል ፣ ከዕውነት የራቀ አይሆንም:: የልዩነታቸው ዕመርታ በጉልህ ሊከሰት የቻለው፣ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1952 ዓም ፤ ግብፅ በሀገር ወዳድ የጦር መኮንኖቿ አማካኝነት የፋሩቅን ዙፋናዊ መንግሥት አስወግዳ የሪፑብሊክ መንግሥት ከመሠረተችና የእንግሊዝን የእጅ አዙር አገዛዝ ከሀገሯ ካባረረች በኋላ ነበር:: ሥልጣን የጨበጡት የጦር መኮንኖቿም ሀገር ወዳድነታቸው እጅግ የላቀ ስለነበር፣ ትኩረታቸው በሀገራቸው ዘላቂ ጥቅምና በሕዝባቸው የኑሮ ደረጃ ዕድገት ላይ ነበር:: በመሆኑም ከሁሉ አስቀድመው ዐባይን መገደብ

ነበረባቸው:: ታላቁን የአስዋን ግድብ ገድበው፣ የዐባይን ውሀ በሚገባ መጠቀም ነበረባቸው:: ሕዝባቸውንም ከረሀብ ከቸነፈር አድነው፣ ጥሩ ተመጋቢ አድርገውታል:: ለስድሳ ዓመታት የተፈራረቁት ሦስት መንግሥታት አንዱ በሰራው ላይ መገንባት እንጅ፣ አንዱ የገነባውን ሌላው የሚያፈርሰው አልነበረም:: በመሆኑም፣ የዛሬ ስድሳ ዓመታት ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ሁኔታ የነበሩት ኢትዮጵያና ግብፅ፣ ዛሬ ያለቡት ሁለንተናዊ ደረጃ ሲታይ፣ የሰማይ የምድር ያህል ተራርቆ ይገኛል:: ለዚህም እንደ ትልቅ ማስረጃ የሚጠቀሰው፣ ከላይ እንደተዘረዘረው፣ ግብፅ ዛሬ ወደ ኒኩሌር ዘመን ስትጠጋ፣ ኢትዮጵያ ግን ሕዝቧን መመገብ የማትችል መሆኗ ብቻ ሳትሆን ፥ የሕዝቧ አንደነትና የራሷ ህልውናም እንኳን ሳይቀር በአደጋ ላይ መውደቁም ጭምር ነው:: ይህ ደግሞ ከላይ ከሰማይ የመጣ ትዕዛዝ ወይም መርገም፣ ሳይሆን ፣ ወይም ደግሞ፣ ግብፆች ከኢትዮጵያውያ የበለጠ ጭንቅላት ኖሯቸው ሳይሆን፥ የግብፅ መሪዎች፣ ከእኛዎቹ በተሻለ ሁኔታ የሀገራቸውን ዘላቂ ጥቅም ያስቀደሙ በመሆናቸው ብቻ ነው::

ወደ እኛው ሀገር ስናተኩር ሁኔታው የተለየ ነበር:: አሁንም ያው ነው:: እንደ ግብፆቹ ሁሉ፣ እኛም በአለፉት ስድሳ ዓመታት፣ ሦስት መንግሥታት ቢቀያየሩም፣ ቢለዋወጡም፣ የሀገራችን ሁኔታ በመሠረታዊ መልኩ ምንም ለውጥ አላገኘም:: ዕርግጥ ግብፅ ለሠላሳ ዓመታት በጦርነት ላይ ብትቆይም፣ እኛም ለአለፉት አርባ ሰባት ዓመቶች በጦርነት ላይ ነበር :: አሁንም ከጦርነት አባዜ ልንላቀቅ አልቻልንም:: ፍጅቱ፣ አለመረጋጉቱ፣ ለልማት ለዕድገት የሚያመች ሁኔታ አለመኖሩ፣ ጭቆናው፣ ስደቱ፣ ረሀቡ፣ ድኅነቱ፤ በሽታው መከራው አሁንም የሕዝባችን የተለመደ ኑሮ መሆኑን ቀጥሏል:: የእነኝህ ሁሉ መሠረታዊ ችግሮች መንስዔዎች፣ ያው ዞሮዞሮ ፀረ ሕዝብ ፀረ ሀገር አምባገነኖች ናቸው:: ይህ ዕውነታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በሚገባ የታወቀ ቢሆንም፣ መፍትሄ ለማግኘት ግን አልተቻለም:: ዘለዓለም፤ ዋይታና ለቅሶ ከማዥጎድጎድ አልፎ ተርፎ፣ ብሔራዊ ችግሮቻችንን ለአንዴና ለሁል ጊዜው የምናስወግድበት፣ ዘለቄታ መፍትሄ ማግኘት ተስኖናል:: ለማነኛውም ሀገር ምንነትና ማንነት ዋስትና የሀገሩ ሕዝብ መሆኑ ባያከራክርም፣ ያን ሕዝብ የሚመራው መንግሥት ግን በማነኛውም መስፈርት ቢመዘን ፣ ለሁሉም ነገር፣ ማለት ለጥፋቱም ይሁን ለልማቱ፣ ለሠላሙም ይሁን ሠላም ለማጣቱ፣ ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታል:: በኃላፊነትም ይጠየቃል:: ሀገር ወዳድ መሪ ነው ተብሎ ለመጠራት ቢሞክርም፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስካልተመሠረተ ድረስ፣ ሀገር ይለማል፣ ሕዝብ ይበለጽጋል፣ ሠላም ይሰፍናል፤ ዕድገት ይገኛል፤ ወንዞች ይገደባሉ፣ መሠረተ ልማቶች ይስፋፋሉ፣ የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ምጥቀት ይመጣል ተብሎ አይታሰብም::

ስለ፣ታላቁ ዐባይ፣ ስለ ታሪካዊው ዐባይ፣ የዓለም ታሪክ መመዝገብ ከጀመረ አንስቶ፣ ብዙ፣ እጅግ ብዙ ተጽፎለታል ተቀኝቶለታል፣ ተገጥሞለታል:: አያሌ ታሪክም ተመዝግቦለታል:: ከታለቁ

መጽሐፍ እስከ ዘመናዊ የፖሊቲካ ትንታኔ ተሰብኮበታል፡፡ ተሰብኮለታል፡፡ በአንድ አካባቢም ተመልኮበታል ፡፡ በዘመናት ፣ ኮከብ ቆጣሪዎች ፤ የውሀ ጠበብቶች
(ሀይድሮሎጅስቶች) ሀገር አሳሾች ( ኤክስፐሎረርስ) የጅግራፊ ጠበብቶች ተመራምረውበታል፣ ደራሲያን ባለቅኔዎች ተቀኝተውበታል፡፡ ዐባይ ሞኙ ሆይ ብለውታል ፡፡ ግብፆችም በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ ሕይወታቸው በዐባይ መኖር አለመኖር መሆኑ በሚገባ ስለተረዱም፣ ዐባይ ወይም ሞት የሚለው መርኅ፣ የኑሯቸው፣ የዕድገታቸው፣ የኢኮኖሚያቸው፣ የደህንነታቸው፣ የውስጥና የውጭ ፖሊሳቸው መሠረት ነው፡፡ ዐባይ፣ ለግብፅ ሕይወት አልፋ - ኦሜጋ መሆኑ በሚገባ ያውቃሉ፡፡ ዕውነትም ዐባይ ለግብፆች ህይወት አልፋ ኦሜጋ ነው፡፡ ወደፊት የዐባይ አካባቢ ሀገሮች ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የውሃው መጠን እየቀነሰ ሲመጣ፣ በአካባቢው፣ ሊያስከትል የሚችለውን ፣ የፖለቲካ ለውጥ ችግር፣ በሚገባ አጢነው፣ ዛሬ የግብፅ መሬዎች የኒኩሌር ኃይል ባለቤቶች ሊሆኑ የሚያበቃቸው ዝግጅትና ጥረት ማድረጋቸው አያስደንቅም፡፡ ወደፊት የኑክሌር መሳሪያቸውን ይጠቀሙበት አይጠቀሙበት ሌላ ጥያቄ ነው፡፡ ግን የኒኩሌር ኃይል ባለቤቶች ለመሆን መወሰናቸው፣ሌላው ቢቀር እኛ ኢትዮጵያውያን ልንጠራጠር የሚገባን አይመስለንም፡፡ ሊያስገርመንም አይችልም፡፡ ዘለአለም ሊያስገርመን የሚችለው ግን የእኛው የራሳችን ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ አሁንም ገና ስለራሳችን ፣ ስለሀገራችን ስለወደፊቱ ዕድላችን ማሰብና መብተክተክ አለመጀመራችን ፤ ከራሳችን አልፎ ተርፎ፣ ዓለምንም ማስገረሙ ቀጥሏል፡፡ የሀገሩን ሕዝብ መመገብ አስመልክቶ፣ በውጭ ርዳታ ምፅዋት ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ የሚያራምድ ከወያኔ በስተቀር በዓለም ውስጥ ማንም መንግሥት ዛሬ የለም፡፡ ዐባይን ተጠቅመን ከድኅነት መውጣታችን ቀርቶ፣ ወደፊት ዐባይ ጠፍቶ እኛንም እንደሚያሰጠፋን መጠራጠር መጀመር አለብን ፡፡ የውጭ ጠላቶች ሊያጠፉት እየተዘጋጁ፣ እርስ በርሱ የሚጠፋፋ ሕዝብ ማለት አትዮጵያውያን ናቸው ከመባል መዳን ይኖርብል፡፡ ይህን ከማሰባችን አስቀድሞ ግን ፣ ለዚህ ተግባር የሚያበቃ ቅድመ-ዝግጅት ማድረግ አለብን ፡፡ ለዝግጅታችን ሁሉ መሠረቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብቶ ሀገር ወዳድ፣ ሕዝብ አፍቃሪ ለህግ ተገዥዎች የሚሆኑ መሪዎች መምረጥ ነው፡፡ መልካም አስተዳደርና ፍትኅ-ርትዕ የሰፈነባት ሀገር እንድትኖር መጣር ነው፡፡ ያ ሳይሆን ቀርቶ፣ “ ዐባይም ቢሞላ፣ ቢሞላ፣ መሻገሪያው ሌላ” እያልን እራሳችንን ብንደልል፣ ዐባይ ራሱ ጠፍቶ እኛንም ከማስጠፋት አያድነንም፡፡ ዐባይን አድነን ፣ እራሳችንንም ለማዳን ከፈለግን ፣ የዛሬዎቹን ፀረ ሕዝብ-ፀረ ሀገር ወያኔዎች ለመጣል ተባብረን ከመስራት የተሻለ አማራጭና አንገብጋቢ ብሔራዊ ግዳጅ አይገኝም፡፡ “ዐባይ ይገደባል፣ ሕዝቡም ይመገባል” ከሚለው የተስፋ መፈክር ባሻገር ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት መታገል የወቅቱ ተግባራችን መሆኑን ለአንድ አፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም፡፡ የግብፅ መንግስታት የዐባይን ጥቅም ሰላወቁ ሶማሊያን ሱዳንንና ተገንጣይ ክፍሎችን ሁሉ እያገዙ እየረዱ ኢትዮጵያ ሰላም እንድታጣ ፤ እንድትዳከም ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ዛሬም በዚሁ መንፈስ ቀጥለዋል፡፡ ግብፅ የወያኔ ደጋፊ

እንደነበረችም መዘንጋት አንችልም፡፡ ወያኔም ውለታ ከፋይ ሆኖ እነሆ ዛሬ ኢትዮጵያን እያዳከመ እየበታተነ--ማለትም ለግብፅ እያገለገለ ነው፡፡ ዐባይን ለሀገር ልማት ለማዋል ከተፈለገ፣ በቅድሚያ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ማስወገድ ይኖርብናል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ተባብሮ መታገል ብቻ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

JULY 22/2009

# SABRE RATTLING BY EGYPT CANNOT PASS

**The traitorous regime of Meles Zenawi has once again ceded Ethiopia's rights over the River Nile. 85% of the water of the Nile comes from the Blue Nile (Abbai River) in Ethiopia.**

**As parliamentarians from 11 African Nile basin countries consider to file a lawsuit against Egypt regarding the 1929 and 1959 agreements that gave it exclusive right on the usage of the Nile, the sold out regime in Addis Ababa, like Egypt's ally Sudan, has reportedly declined to back the riparian countries. The 1929 agreement was signed between Egypt and colonial Britain without the participation of Ethiopia or any other riparian country. In 1959 Sudan and Egypt signed an amendment to the 1929 document and once again gave full rights to Egypt over the Nile to the detriment of the interests of the African countries concerned. Last month, the Nile Basin countries met in the Congo to discuss a more rationale use of the Nile but Egypt refused to sign the common document alleging that come what may it will defend its so called "historical rights". Back in 1993, the Meles regime reportedly signed an agreement with Egypt ceding Ethiopian rights and by refusing now to join the 11 countries trying to bring the case against Egypt and Britain to the International Court of Justice (ICJ) it has proved beyond any shadow of a doubt its anti Ethiopian nature.**

**Egypt's greedy claim over more and more of the waters of the Nile has hindered the other countries from using the Nile waters for their own irrigation and farming. At the Congo meeting Egypt wanted the African countries to approve its "right to 5.5 billion cubic square metres of waters annually" as well as to agree that dam or other project will not be done on the Nile without Egyptian approval and that the Convention be amended only by unanimous vote. Egypt has grandiose plan to use the water of the Nile to develop a desert area to be populated by millions of settlers. To assure supremacy of its demands Egypt has tried several invasions and sabotage**

directed against Ethiopia and the late Sadat had even threatened war against Ethiopia over the Nile. The sabre rattling has now been taken by Al Ahram news paper and other Egyptian officials who are now declaring they will go to war if Egypt's so called rights are compromised.

The traitorous regime of Meles Zenawi has undoubtedly ceded Ethiopia's rights to Egypt. Yet, Ethiopians will not relinquish their historical rights to the Nile whose waters come mainly from Ethiopia. The EPRP backs the 11 African countries' attempt to take Egypt and Britain to the ICJ and their demand to have the unfair and illegal treaties of 1929 and 1956 abrogated.

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France